

## መንግስቱ ንዋይ : መጋቢት 19 ፣ 1953 ዓ.ም የሞት ፍርድ ከተወሰነባቸው በኋላ የተናገሩት ንግግር

እናንት ዳኞች የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለ ይግባኝ ተቀብያለሁ፡ ይግባኝ ብዬ ጉዳየን የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ህዝብ ቢሆን ኖሮ ይግባኝ ማለት በፈለግሁ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ እንደሚይሆን አውቃለ ወና በይግባኝ የአፄ ኃ/ስላሴን ፊት ማየ ት አልፈቅድም፡ በእግዚያብሄር ስም ተሰይማችሁ ከተቀመጣችሁብት የፍርድ ወንበር ላይ ከመቀመጣችሁ በፊት በእኔ ላይ የምትሰ ጡትን የዛሬወን ፍርድ ታውቁት እንደነበር ሳስብና ፍርድ እስከዚህ መርከሱን ስ ታዘብ ሀዘኔ ይበዛል፡፡ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነ ት፣ ነፃነትና እርምጃ የተነሳሁ ወዳጅ ነኝ እንጅ ለማፉጀት የተነሳሁ ወንበዴ አይደለሁም፡ ይህንን ማድረግ ፈልጌ ቢሆን ኖሮ ማን ም የሚይወዳደረ ው ሰራዊትና መሳሪያ ሳላጣ ዛሬ እዚህ ከእናንተ ፊት ለመቆም ባልበቃሁ ነበር፡፡ እኔ ከየአፄ ኃ/ስላሴ ድንክ ወሾች ያነሰ ደመወዝ የ ሚያገ ኙ ሁለት የተራቡ ወታደሮችን አጣልቼ ለሚደባደብና አገር ለማፍረስ አለመምጣቴን የ ሚያረጋግጥልኝ እናንተ በትዕዛዝ ያገኛችሁትን ፍርድ ለመቀበል እዚህ መቆ ሜ ነ ው፡ ከእኔ በፊት በግፍ የፈሰሰ ውንፀህ የኢትዮጵያዊያን ደም ብዙ ነ ው፡ በየአፄ ኃ/ስላሴ ዘመ መንግስት ግፍ ሽልማት በመሆኑ እኔ ለመሞት የ መጀመሪያ ው ሰ ው አልሆንም፡ ስልጣን አላፊ ነ ው፡ እናንተ ዛሬ ከ ጨበ ጣችሁት የበለ ጠ ስልጣን ነበረኝ፡፡ ሀብትም አላ ጣሁም፡ ነገር ግን ህዝብ የ ሚበደልበት ስልጣንና ደሃ የ ሚይካፈለ ው ሀብት ስላልፈለግሁ ሁሉን ም ንቄ ተነሳሁ፡ አሁን ም እሞታለሁ፡ ሰ ው ሞትን ይሸሻል ፡፡ እኔ ግን በደስ ታ ወደ ሞት እሄዳለሁ፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅነ ት ቀድመውኝ መስዋዕት የሆኑትን አብሪ ወኝ ተነ ስተው የነበሩትን ጀግኖች ወን ድሞቼን ለማናኘት ናፍቄአለሁ፡ የጀመር ኩት ስራ ቀላል አይደለም፡ አልተሸነ ፍኩም፡ ወነ ኔ የሆ ው ድሃ ው የኢትዮጵያ ህዝብ የጀመር ኩለትን ስራ በቅርብ ጊዜ ወስ ጥ ፈፅሞ ራሱን በራሱ እንደ ሚጠቅም አልጠራጠር ም፡ ከሁሉ በበለ ጠ የ ሚያስደስተኝ ለኢትዮጵያ ህዝብ ልሰ ራለት ካሰብኳቸው ስራዎች አንዱ የኢትዮጵያ ወታደር ዋጋና ክብር ከፍ ማድረግ ሲሆን ይህ ሃሳቤ ህይወቴ ከማለፉ በፊት ሲፈፀ ም ማየ ቴ ነ ው፡ ዛሬ መኖ ራችሁን በማየ ቴ ነገ መሞታችሁን ረስ ታችሁ አ ሜኬ ብላችሁ ቀናችሁን በማስተላለፍ በማ ደዳችሁ በእኔ ላይ ሳትፈር ዱ በራሳችሁ ላይ የፈረዳችሁ መሆናችሁን አላስተዋላችሁም፡ እኔ የተነሳሁት ከትክክለኛ ህግና ከህሊናችሁ ውጭ ለ መፍረ ድ እንዳትገ ደዱ ለ ማድረግ ነበር፡፡ በአ ጭሩ በእኔ ላይ ለ መፍረ ድ የቸኮላችሁትን ያህል አስር እና አስራ አምስት ዓመት በቀ ጠሮ የ ምታጎላሉትን ህዝብ ጉዳይ እንደዚህ አፋጥናችሁ ብትማለከቱትና ብትሸ ኙት ኖሮ የእኔ ማ ሳት ባላስፈለገ ም ነበር፡፡ ከእናንተ ከዳኞቹና የ ሞት ፍር ድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰ ው ይልቅ እኔ ፍርድ ተቀባይ የዛሬ ወን ጀለኛ የነገ ባለ ታሪክ ነኝ፡ የኔ ከ ዳደኞቸ መካከል ለጊዜ ው በህይወት መቆየ ትና ለእናንተ ፍርድ መብ ቃት የ መማዛኑን ፍርድ ለ መጭው ት ውልድ የ ሚያሳይ ይሆናል፡፡ ዋ ! ዋ ! ዋ ! ለእናንተና ለገ ዢአችሁ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ሃሳቤ በዝርዝር ገ ብቶት በአንድነ ት በ ሚ ሳበት ጊዜ የ ሚወር ድባችሁ መዓት አሰ ቃቂ ይሆናል፡፡ በተለይ የአፄ ኃ/ስላሴ የግፍ መን ግስት ባላደራዎች ሆነ ው ድሀ ወን የኢትዮጵያ ህዝብ ሲገ ሸል ጡት ከነበሩት መኮንን ሀ/ወልደና ገ/ወልድ እንግዳወርቅን ከ መሳሰሉት በ መንፈስ የ ታሰሩ በስጋ የኮሰሱ መዝባ ሮች መካከል ጥቂቶቹን ገለል ማድረጌን ሳስ ታውስና የተረፉትም ፍፃ ሜቸ ወን በ ሚ ይደሉት በኢትዮጵያ ህዝብ እጅ ላይ መወደቅ ሲሰ ማኝ ደስ ይለኛል፡፡

ምንጭ፤ ኢትዮ ኮርነርስ

